ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር ………/2016

ጥር 2016

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር …../2016

# የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ

የፌደራል መንግስት የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ 2 ለግብርና ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር ----/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 ነው፤
2) **"የመልካም ግብርና አሰራር"** ማለት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና የግብርና አሰራሮችን የአፈርን ለምነትን በማይጎዱ፣ አከባቢን በማይበክሉ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ጫና በማይስከትሉበት ሁኔታ መጠቀም ነው፤
3) **"የግብርና ቴክኖሎጂ"** ማለት በምርምር የተገኘ በእንስሳት እና ዓሣ፣ በዕጽዋት እና በግብርና ተፈጥሮ ሃብት መስክ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም ጥራትን እና ጤንነትን ለማሻሻል የሚውል ሆኖ በባለስልጣኑ ብቁነቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ወይም በሌላ አገር ተመዝግቦ በግብርና ሚኒስቴር ውሳኔ ቀጥታ የቴክኖሎጂ ስም ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የባህላዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር ግኝት ነው፤
4) **"በሙከራ ደረጃ"** ማለት አንድ የተሻሻለ አሰራር ወይም የግብርና ቴክኖሎጂ በሰርቶ ማሳያ ደረጃ ውጤታማነቱ እስኪረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፤
5) **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ወይም በክልል የግብርና ግብዓትና ምርትን ጥራት የሚቆጣጠር ባለሰልጣን ወይም የመካኒካል ቴክኖሎጂ ወይም ደቂቀ ዘአካላት እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎችን የሚመዘግብ የፌደራል አግባብ ያለው ባለስልጣን ነው፤

6) **"ቴክኒክ ግብረ ኃይል"** ማለት አግባብ ባለው አካል የምርት መጠን ወይም ጥራት መቀነስ ወይም ሙሉ በሙሉ መጥፋት ወይም መጨመር መንስኤዎችን ለማጥናት፤ የግብርና ምርት ውል አሰራር ሙያዊ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ከራሱና ከሶስተኛ ወገን የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የሚደራጅ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ድጋፍ አሰጣጥ ወሰንና አፈጻጸም

### 3. በግብርና ምርት ውል ዓይነት ስለሚሰጠው የድጋፍ ወሰንና አፈጻጸም

1) የግብርና ምርት ውል ዓይነትን መሰረት ተደርጎ የሚሰጥ ድጋፍ በተዋዋይ ወገኖች የጋራ መግባባት መሰረት በውል ሰነዱ ላይ በዝርዝር መቀመጥ አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርት ውል የሚከተሉትን የድጋፍ ዓይነቶች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

3) ስለ ተቀናጀ ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ) አስመራቹ ይዞት ከሚመጣ የግብርና ቴክኖሎጂ እና በራሱ ማሳ ከሚያሳየው የመልካም ግብርና አሰራር የተነሳ በአካባቢው እና በዙሪያው ውል ለተዋዋሉ አምራቾች **የኤክስቴሽን አገልግሎት** መስጠት፤

ለ) ከሰጠው የኤክስቴሽን አገልግሎት የተነሳ ተቀባይነት ያገኙ አሰራሮችንና የግሉ የሆነ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን **በሙከራ ደረጃ** በተመረጡ እና ማዕከላዊ ቦታዎች በሚገኙ ሞዴል አምራቾች በስፋት ማስተዋወቅ፤

ሐ) በስፋት ለተዋወቀው የአስመራቹ የግብርና ቴክኖሎጂ እና የመልካም ግብርና አሰራር በአስመራቹ እና በአምራቹ መካከል በሚደረገው ውል መሰረት **ግብዓቶች እና የቴክኒክ ድጋፍ** መስጠት ነው፡፡

መ) ከዚህ በላይ የተቀመጡትን የድጋፍ ዓይነቶች በሁሉም ወይም በከፊል ለመስጠት ተስማምተው ከሆነ በውላቸው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

4) ስለ ተማከለ ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ) አስመራቹ የራሱን ባለሙያዎች በመቅጠር ወይም የሶስተኛ ወገን በመወከል ቀጥታ ከአምራቾች የግብርና ምርቱን በገባው ውል መሰረት ይሰበስባል፤

ለ) አስመራቹ በሚመድባቸው የራሱ ቅጥር ባለሙያዎች ውል ለገባው አምራች በአመራረት እና ርክክብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ የምርት ጥራት ቁጥጥር ሥራዎችንም ይሰራል፤

ሐ) አስመራቹ በአምራቾች አጠገብ የምርት ማዘጋጃ እና ማከማቻዎችን መገንባት ወይም ከሶስተኛ ወገን በኪራይ ማመቻቸት፤

መ) ፊደል ተራ ሐ እንደተጠበቀ ሆኖ አስመራቹ ምርቱ ከተመረተበት አካባቢ ወይም ቦታ ወደ ማዘጋጃው እና ማከማቻ ቦታ በቀጥታ ማጓጓዝ፤

ሠ) አስመራቹ ከአምራቹ ጋር በሚገባው ውል መሰረት ግብዓቶችንና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

5) ስለ ባለብዙ ተዋንያን ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ) የባለብዙ ተዋንያን ውል ዓይነት የግብርና ምርት ውልን የሚደግፉ መንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን ያካትታል፤

ለ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ “ሀ” የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን የመንግስትና የግል የግብርና ምርምር ተቋማትን፣ ዩኒቨርስቲዎችን፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎችን፣ የፋይናንስ ተቋማትን፣ አማካሪዎችን፣ የሲቪክ ማህበራትና ድርጅቶች፤ የዘርፍና የሙያ ማህበራት፣ ሕብረት ሥራ ማህበራትን ድጋፍ ሰጪ ተቋማትን ያካትታል፤

ሐ) ለተዋዋዮች ድጋፍ የሚሰጡ መንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን ተዋንያን የድጋፍ አሰጣጥ ሂደቱን ውጤታማ የሚያደርግ የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማሉ፤

መ) በመግባቢያ ሰነዱ የሚሳተፍ ማንኛውም መንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን በመግባቢያ ሰነዱ ለተዋዋዮች ስለሚያደርገው የፋይናንስ፣ የቴኖሎጂ፣ የማማከር፣ የግብዓት፣ የስልጠና እና የሙያ የድጋፍ ዓይነቶች በግልጽ ማስቀመጥ አለበት፤

ሠ) በድጋፍ አሰጣጡ ሂደት አግባብ ያለው አካል ሊኖረው ስለሚገባ ድርሻ በመግባቢያ ሰነዱ በግልጽ መቀመጥ አለበት፤

ረ) የመግባቢያ ሰነዱን አግባብ ያለው አካል ከተዋዋይ እና መንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤

ሰ) የመንግስታዊ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶችን ሚና የተዋዋዮችን ውል በሚጣረስ መንገድ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ያለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

6) ስለ አገናኝ ውል የድጋፍ አሰጣጥ

አገናኝ አምራቹን ሙሉ በሙሉ ወክሎ ከአስመራች እና ከሶስተኛ ወገን ጋር የመደራደር እና የመዋዋል መብት በገደብ የሚሰጠው ነው፤ በዚህም መሰረት አገናኙ፡-

ሀ) ህጋዊ የግል ወኪል፤የህብረት ሥራ ማህበር፣ የዘርፍና የሙያ ማህበራት፣ የግል እና የመንግስት የትምህርት ተቋማት፣ የመንግስትና የግል የምርምር ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራትና ድርጅቶች ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን አገኛኝ ሊሆን ይችላል፤

ለ) አምራቹ እንዲወክለው የወሰነውን አገናኝ ህጋዊነት አስመልክቶ ለአስመራቹ በቂ ማስረጃ ወይም መረጃ መስጠት አለበት፤

ሐ) አምራቹን የሚወክለው አገናኝን ሚና ወሰን በተመለከተ ተዋዋዮቹ በውላቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

መ) አገናኝ ስለሚኖረው ሚና መወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ አምራች ከአስመራቹ ማግኘት በሚገባው ግብዓትና የቴክኒክ ድጋፍ ላይ አሉታዊ ሚና መጫወት የለበትም።

4. በሶስተኛ ወገን ስለሚሰጥ የድጋፍ ዓይነትና የአፈጻጸም መሰፈርት፡

በአዋጁ አንቀጽ 16 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአምራቹ የሚሰጡ ማበረታቻዎች የግብርና ምርታማነትን እና ጥራትን የሚያሳድጉ ግብዓቶችን ነው።

1) ለአስመራቹ በሶስተኛ ወገን ወይም አግባብ ባለው አካል የሚሰጡ ማበረታቻዎች በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

ሀ) ለውጭ ገበያ ያቀረበው የግብርና ምርት መጠን እና ጥራት፣

ለ) ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የሚተካ ለአገር ውስጥ ገበያ ያቀረበው የግብርና ምርት መጠን እና ጥራት፣

ሐ) ያሳተፋቸው አምራቾች አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች በተጨማሪ የሴቶች/ወጣቶች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ከግምት ያስገባ ቁጥር ብዛት፣

መ) ለአርሶ አደሮች የሚጠው የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት እና ያስፋፋው አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ፣

ሠ) ያመቻቸው የሥራ ዕድል እና የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎ፣

ረ) ምርትና ምርታማነት ማሳደግ መቻሉ፣

ሰ) የመረጃ አያያዝ እና ተደራሽ ለማድረግ ያሳየው ትብብር።

## ክፍል ሦስት

## ውልን ስለሚለውጡ ሁኔታዎች

5. የምርት ዋጋ ሲጨምርና ሲቀንስ፡-

በምርት ርክክብ ጊዜ በውሉ ከተገለጸው በላይ ዋጋ ሲጨምርና ሲቀንስ ስለሚደረጉ ማሻሻያዎች፡-

1) የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሁኔታ በውሉ ላይ በግልጽ አስቀምጠው ከሆነ በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

2) ወቅታዊ የማምረቻ እና የገበያ ወጪ፣ የምርት ሽያጭ ዋጋን ግምት ውስጥ በማስገባት የምርት ዋጋን ለመወሰን የሚያስችላቸውን ድጋፍ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ይሰጣሉ፤

3) የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ዝርዝር ሁኔታ በውላቸው ላይ ካላስቀመጡ ግን በሚከተሉት ሂደቶች መሰረት የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፤

ሀ) በወቅታዊ ዋጋ ላይ ልዩነት ሲኖር ሁለቱ ወገኖች በጋራ በመነጋገር በስምምነት መፍታት ይችላሉ፣

ለ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጡት አንድ የጋራ አደራዳሪ አማካኝነት ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፣

ሐ) ከላይ በፊደል ተራ "ለ" በተገለጸው መሰረት በአደራዳሪው አማካኝነት መግባባት ላይ ካልደረሱ ተደራዳሪዎቹ የየራሳቸውን አንድ አንድ ሰው መርጠው የሚመለከተው አግባብ ያለው አካል ሊያደራድራቸው ይችላል፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ እስከ ሐ" በተደነገገው ሰምምነት ላይ ካልደረሱ በአዋጁ መሰረት በፍርድ ቤት ይዳኛሉ።

## 6. የምርት መጠን ሲቀንስ ወይም ሲጨመር

1) በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ በውሉ የተጠቀሰው ምርት መጠን ቢቀንስ አምራቹ ውል እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ) በአስመራቹ የተሰጠውን የግብርና ቴክኖሎጂ መጠቀም ትቶ ከውሉ ውጭ ሌላ የተጠቀመ እንደሆነ፣

ለ) በአስመራቹ በተሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ መሰረት ሳይጠቀም ሲቀር፣

ሐ) ምርቱን ከሰበሰበ በኋላ ሆን ብሎ ለራሱ ሲያስቀር ወይም ለሌላ ወገን ሲሸጥ፣

መ) በአስመራችና አምራች ውል የተጠቀሱና በአምራቹ ሊተገበሩ የሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮች ሳይተገበሩ ሲቀሩ፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

2) በሚከተሉት ምክንያቶች በውሉ ከተጠቀሰው በታች ምርት ቢቀንስ አስመራቹ ውል እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ) ለአምራቹ የሰጠው የግብርና ቴክኖሎጂ በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ያልተመዘገበ ወይም ውጭ ሀገር ተመዝግቦ በሀገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፣

ለ) ለአምራቹ የሰጠው የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ተባይ ወይም በሽታ መከላከያ መድሃኒት በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ወይም ውጭ ሀገር ተመዝግቦ በሀገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ፣ ያልተመዘገበ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፣

ሐ) ለአምራቹ ሊሰጠው የሚገባ የግብዓት ወይም የቴክኒክ ድጋፍ በግብርና ምርት ውሉ በተቀመጠው ጊዜ፣ ጥራት እና በሚፈለገው መጠን ልክ ሳይሰጥ ሲቀር፣

መ) አስመራቹ በስነልክ ኢንስቲትዩት አግባብነታቸው ያልተረጋገጠ ሚዛን ወይም ሌላ መለኪያ በመጠቀሙ፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ኃይል የተነሳ ምርትና ምርታማነት ቢቀንስ በአዋጁ አንቀጽ "17" መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

4) የምርት መጠን በሚከተሉት ምክንያቶች አምራቹ ጨምሮ ሲገኝ ውል እንደተጣሰ ይቆጠራል፤

ሀ) በውል ከተያዘው ማሳ ውጭ የተሰበሰበ ምርት ከተጨመረ፤

ለ) የግብርና ምርት ማምረት ውልን ዓላማን በሚጻረር መልኩ ምርት እንዲጨምር ከተደረገ፤

5) አምራች አስመራች ባልገመተው ሁኔታ ሙሉ የአመራረት ምክረ ሃሳብ ጥንቅርና አሰራር ተጠቅሞ ውል ከተገባው ምርትና ምርታማነት ጨምሮ ቢገኝ አስመራች ስለሚረከብበት ሁኔታ በውሉ መካተት አለበት።

## 7. የምርት ጥራት ሲጓደል የውል አፈጻጸም ሁኔታዎች፡-

ለምርት ጥራት መጓደል መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ በግብርና ምርት ውል ውስጥ ማካተቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) በሚከተሉት ምክንያቶች የምርት ጥራት መጓደል ቢከሰት አምራቹ የግብርና ምርት ውሉን እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ) በሃገሪቱ የግብዓትና ምርት ጥራት ደረጃዎች መሰረት ጥራት የሚያጓድሉ ተብለው ከተፈላጊው ቁስ የተለዩትን ሁሉ በግብርና ምርቱ ውስጥ ከተጨመረ፣

ለ) ውሃ በመጨመር የተፈቀደው የተፈጥሮ የእርጥበት መጠን ወይም ይዘትን ካዛባ፣

ሐ) ከተፈቀደው የግብርና ምርት መያዣ ወይም መሰብሰቢያ ወይም ማከማቻ ወይም ማጓጓዣ ወይም ማቀዝቀዣ ውጭ ምርቱን በማስቀመጡ ወይም በማጓጓዙ ጥራት ሲያጓድል፣

መ) ተገቢውን የጸረ ተባይ ወይም የበሽታ መከላከያ መድሃኒት ባለመጠቀሙ የምርቱ ጥራት ቢጓደል፣

ሠ) ያልተፈቀደ ወይም በተዋዋይ ወገኖች በግብርና ምርት ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ይዘት እና ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል ከተጠቀመ፣

ረ) ሌሎች በግብርና ምርት ውሉ የተጠቀሱ ወይም በተክኒክ ድጋፍ ወቅት በጽሁፍ የተገለጹ ጥራትን ሊጠብቁ የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦች በአምራቹ በኩል ተግባራዊ ሳይሆኑ ሲቀሩ፤

ሰ) በውሉ ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ምርቱን ለአስመራቹ ባለማስረከቡ በሚደርስ የምርት ጥራት መጓደል፣

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከ “ሀ” እስከ “ሰ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

2) በሚከተሉት ምክንያቶች የምርት ጥራት መጓደል ቢከሰት አስመራቹ የግብርና ምርት ውሉን እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ) በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችሉ ግብዓቶች ለአምራቹ ሳያቀርብ በመቅረቱ፣

ለ) በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ ለአምራቹ ሳይሰጥ ቢቀር፣

ሐ) ያልተፈቀደ ወይም ግዜ ያለፈበት ወይም በግብርና ምርት ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል አምራቹ እንዲጠቀም ካደረገ፣

መ) በውሉ በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ተገኝቶ ምርቱን ከአምራቹ ባለመረከቡ በሚደርስ የምርት ጥራት መጓደል፣

ሠ) ሌሎች ጥራትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እና በግብርና ምርት ውሉ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈጽም ቢቀር፣

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ “ሀ” እስከ “ሠ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋር የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

## 8. ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሲፈጠር የማሳወቂያ ሂደት አፈጻጸም እና የግዜ ገደብ

ከግብርና ምርት ተዋዋይ ወገኖች በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት ክስተቶች በተፈጠረ ጊዜ፡-

1) ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን እና ለሚመለከተው አግባብ ያለው አካል በ 72 ሰዓት ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ ማሳወቅ ይኖርበታል፣
2) የተከሰተውን ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በስልክ፣ በኢሜል፣ በጽሁፍ ወይም በአካል ማሳወቅ አለበት፤
3) በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባዉን ግዴታ መፈጸም የማያስችለዉ መሆኑን አግባብ ያለዉ አካል በቴክንክ ግብረኃይል ሊያረጋግጥ ይገባዎል፤
4) የተከሰተውን የጉዳት መጠን ለመወሰን ሁለቱ ወገኖች በጋራ በመነጋገር በስምምነት መፍታት ይችላሉ፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "4" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጡት አንድ የጋራ አደራዳሪ አማካኝነት ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፤
6) በዚህ አንቀጽ **ንዑስ አንቀጽ "5"** በተገለጸው መሰረት መግባባት ላይ ካልደረሱ ተዋዋዮች የየራሳቸውን አንድ ሰው መርጠው ሦስተኛ ወገን በተገኘበት አግባብ ያለው አካል ሊያደራድራቸው ይችላል፤
7) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ቁጥር "4 እስከ 6" በተደነገገው ስምምነት ላይ ካልደረሱ በአዋጁ መሰረት በፍርድ ቤት ይዳኛሉ።

## 9. የምርት ርክክብ እና የክፍያ ሁኔታ

1) የምርት ርክክብን አስመልክቶ የመረካከቢያ ቦታ እና ጊዜን በውል ሰነዱ ላይ በዝርዝር በማስቀመጥ በውላቸው መሰረት ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## ክፍል አራት

## የግብርና ምርት ውል ተሳተፊዎች መስፈርት እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ

### 10.የተዋዋይ ምልመላ መስፈርት

1) የአስመራች መመልመያ መስፈርት
   ሀ) የግብርና ምርት ለማስመረት ፍላጎት ያለው፣
   ለ) በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ማቅረብ የሚችል፣
   ሐ) የግብርና ምርት ውል ኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው፣
   መ) በግብርና ምርት ውል የሚሳተፉበት የሀብት መጠን የሚገልጽ የ6 ወራት የባንክ ስቴትመንት እና በውጪ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ ሪፖርት፣

ሠ) የንግድ ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚችል፣

ረ) ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የመስጠት አቅምና ፍላጎት ያለው፣

ሰ) ግብአት የማቅረብ አቅምና ፍላጎት ያለው፣

ሸ) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረት እና ለመግዛት ከሚገባው ምርት ጠቅላላ የመግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ስለማስያዙ፤

ቀ) በግብርና ምርት ውል ትስስር ለተሳተፉ አምራቾች ወቅታዊ ስልጠናዎችን በመስጠት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን የሚችል፤

በ) በገባው ውል መሰረት ክፍያ መክፈል የሚችል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2) የአምራች መመልመያ መስፈርት

ሀ) በግብርና ምርት ውል ትስስር ለመሳተፍ ፈቃደኛና ታማኝ የሆነ፣

ለ) ህጋዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለው ወይም ህጋዊ የሆነ ቢያንስ የአንድ ዓመት የመሬት ኪራይ ውል ያለው ፤ ለቋሚ ሰብሎች እንደየሰብሉ አመራረት ባህሪ ተለዋዋጭ ቢሆንም ቢያንስ አስር አመት የመሬት ኪራይ ውል ያለ

ሐ) የግብርና ዕውቀትና ልምድ ያለው፣

መ) ለመማር ወይም ትክክለኛውን ምክረ-ሃሳብ ተከትለው ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፤

ሠ) ምርታቸውን በገቡት ውል መሰረት በጥራት ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆነ

ረ) ለምርት ጥራትና መጠን የሚያስፈልጉ /በአስመራች የሚቀርቡ/ ግብዓቶችና የቴክኖጂ ውጤቶችን በአግባቡ ለመጠቀም ፍቀደኛ የሆነ

ሰ) የጋብቻ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

ሸ) ህብረት ሥራ/ዩኒየን ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው፤

## 11.የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ

የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ በሁለት መንገዶች የሚከናወን ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ተቀምጧል፤

1) በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

አንድ ሰው በግብርና ውል ተመስርቶ የግብርና ምርትን ለማስመረት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች እንዲስማራ ሲጠይቅ የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡-

ሀ) በግብርና ምርት ውል ለመሳተፍ በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ለግብርና ሚኒስቴር ማመልከቻ ሲያቀርብ፣

ለ) የግብርና ምርት ውል ኢንቨስትመንት ፍቃድ፣

ሐ) የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣

መ) ስራውን በሚሰራበት ክልል ወይም በፌደራል ደረጃ ቢሮ ሲኖረው፤

ሠ) የ6 ወራት ባንክ ስቴትመንት እና የውጪ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ፤

ረ) የንግድ ዕቅድ ማቅረብ የሚችል፤

ሰ) ለህበረት ሥራ ማህበራት ሲሆን የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

ሸ) በሚሰማራባቸው ክልሎች አግባብ ባለው አካል እና ውልን ለመመዝገብ በተፈቀደልት አካል የተፈረመና ማህተም ያረፈበት የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ ለግብርና ሚኒስቴር ማቅረብ የሚችል፤

ቀ) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረት እና ለመግዛት ከሚገባው ምርት መጠን ጠቅላላ የመግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ማስያዙ፤

## 12. የሚኒስትሩ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ አዘገጃጀትና ይዘት

ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች በግብርና ምርት ውል ተመስርቶ ለማስመረት ለሚሰማራ ሰው የሚዘጋጀው የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ በአወጁ አንቀጽ 5 እና 6 ላይ የተጠቀሰው የግብርና ምርት ውል አዘገጃጀት እና ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፤

ሀ) አስመራች የግብርና ምርት ውል የገባባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች ዝርዝር ለክልል አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤

ለ) የግብርና ማምረት ተግባሩ የሚከናወንበት ቦታ አድራሻ የሚያሳይና በጂፒኤስ የተደገፈ ካርታ ለክልል አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤.

ሐ) በውሉ የተካተቱ አምራቾች ብዛትና ውል የገቡበት የማሳ ስፋት፣ ግብርና ምርት ዓይነት፤ መጠንና የጥራት ደረጃ ማጠቃለይ የሚያሳይ መረጃ በክልል በኩል መቀረቡን፤

መ) የግብርና ምርት ውሉ ዓይነት እና ሚኒስቴሩ በማጠቃለያ ቅጹ የሚያካትታቸው ሌሎች መረጃዎች፤

# ክፍል አምስት

## የውል ሀሳብ መመርመሪያ ጊዜ

## 13.የግብርና ምርት ውል ሃሳብን ለማቅረብና ለመመርመር የሚሰጥ የጊዜ ገደብ

በአዋጁ አንቀጽ 4 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ተዋዋይ ወገኖች የውል መነሻ ሃሳብ ይዞ ለመቅረብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አስቀድመው ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) ማንኛውም ተዋዋይ ወገን የውል መነሻ ሃሳብን ይዞ የሚቀርበው ውል ከሚገባበት የግብርና ምርት ማምረቻ ሥነ ምህዳር አኳያ የዘር ወቅት ከመድረሱ አንድ ወር በፊት መሆን አለበት፤

ለ) የግብርና ምርት ውል መነሻ ሃሳብ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመመርመር የሚወሰደው ጊዜ ከአስራ አምስት ቀናት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

## 14. የግብርና ምርቶች የውል ዘመን፤

ተዋዋይ ወገኖች በውል ሰነዱ የሚግባቡባቸው የግብርና ምርት ውል ዘመን እንደ ሰብሉ የአመራረት እና የሚደርሱበት የጊዜ ሁኔታ የሚለያይ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች በሚከተሉት አግባብ የውል ዘመን ሊወስኑ ይችላሉ፤

ሀ) ዓመታዊ ለሆኑ ሰብሎች የምርት ዘመኑ በሚወስደው ጊዜ ውስጥ የሚወሰን ይሆናል፣

ለ) የሕይወት ዑደታቸውን ለመጨረስ ከአንድ ዓመት በላይ (ሰንባች ሰብሎች) የሚፈልጉ የግብርና ምርቶች ወይም በባሕሪያቸው ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን የሚያስፈልጋቸው ቋሚ የግብርና ምርቶች እንደ ምርቱ ዘመን የሚለያይ ሆኖ የውል ዘመኑ በአምራችና አስመራች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፣

ሐ) ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን የሚያስፈልጋቸው የግብርና ምርቶች ዝርዝር ሚኒስቴሩ ሰፊ ሽፋን ባለው የመገናኛ ብዙሃን ወይም በራሱ የበይነ መረብ አድራሻ ያሳውቃል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 15. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በጣሰ አካል በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው አካል የሚወሰዱ አስተዳደሪያዊ እርምጃዎች፡-

ሀ) አስመራች በአምራቹ ላይ ላደረሰው ጉዳት በውላቸው ላይ በተገለጸው መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ማስደረግ፤

ለ) አምራቹ አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ/አርብቶ አደር ከሆነ በግብርና ውል መሰረት በሚደረገው የአምራችና አሰመራች ግንኙነት በጽሁፍ በሚገለጽ የተወሰነ ግዜ ከግብርና ምርት ውል አሰራር እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤

ሐ) አምራቹ ሰፋፊ እርሻ ያለው ከሆነ በአስመራቹ ላይ ላደረሰው ጉዳት በውላቸው ላይ በተገለጸው መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ማስደረግ፤

መ) አስመራቹ ወይም አምራቹ አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይችል የነበረውን ድጋፍ ወይም ማበረታቻ አንዲያጣ ማድረግ፤

ሠ) ሶስተኛ ወገን ላደረሰው ጉዳት በውላቸው ላይ በተገለጸው መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ማስደረግ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ “ሀ” እስከ “ሠ” የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የሚወስደው አስተዳዳራዊ እርምጃ፤

ሀ) የኢትዮጵያን ሕግ ሁሉ ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ) ከመውሰዱ በፊት የተፈጸመው ድርጊት የግብርና ምርት ውልን፣ አዋጁንና ይህን መመሪያ ያልተከተለ መሆኑና ሌላኛውን ወገን የጎዳ መሆኑን ገለልተኛ በሆነ አካል በጥናት አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፤

ሐ) ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተዋዋይ ወገኖችን ወይም የተዋዋይ ሶስተኛ ወገንን የመደራደር መብት አለመጣሱን ማረጋገጥ አለበት፤

መ) ለሚመለከተው ተዋዋይ ወይም ሶስተኛ ወገን አስቀድሞ ቅሬታውን በጹህፍ መግለጽ አለበት፤

## 16. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ይህ መመሪያ የተደነገገባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 17. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)**

**የግብርና ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**